የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ምዕራፍ 1 እና 2

1. የሮሜ መልእክትን ከሌሎች መልእክታት የሚለየው ምንድን ነው?
ሀ. ከመልእክትነት ይልቅ ዝርዝር የነገረ መለኮት ትምህርት መያዙ
ለ. ሰፋ ያለ የብሉይ ኪዳን መልእክቶችን ማካተቱ
ሐ. ሮማውያን የክርስቶስ ፍጹም አምላክነት እና ፍጹም ሰውነት ላይ ለነበራቸው ጥያቄ መልስ ይሆን ዘንድ መጻፉ
መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. ቅዱስ ጳውሎስ የጻፋቸው መልእክታት ስንት ናቸው?
ሀ. 15 ለ. 20 ሐ. 14 መ. 10

3. ቅዱስ ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት እና ፍጹም ሰውነት ለሮማውያን ያስረዳው እንዴት ነው?
ሀ. ሰው መሆኑን: የእመቤታችን የዘር ሃረግ ከንጉሥ ዳዊት እንደሚመዘዝ በማሳየት
ለ. አምላክ መሆኑን: ሰው ከሞት መነሳት እንደማይችል በማስረዳት
ሐ. አምላክ መሆኑን: መራብ መጠማቱን መታመሙን በማሳየት
መ. ሀ እና ለ

4. የሮሜ መልእክት የተጻፈው ለማን ነው?
ሀ. በሮሜ ላሉ አይሁዳውያን
ለ. በቆሮንቶስ ለሚገኙ የሮሜ ሰዎች
ሐ. በሮሜ ላሉ አሕዛባውያን
መ. ሀ እና ሐ

5. ከሚከተሉት ውስጥ ቅዱስ ጳውሎስ ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ስለነበረው ሕይወት ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ. የደማስቆ ሃገረ ገዢ ነበር
ለ. የህግ እና የኦሪት ተማሪ ነበር
ሐ. የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዝሙር ነበር
መ. ለ እና ሐ